# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት





ሐምሌ 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ

**መግቢያ ........ 1**

ዩኒቨርስቲው የተቋቋመበት ዓላማ ........ 2

የዩኒቨርሲቲው ስልጣንና ተግባር ........ 3

የዩኒቨርሲቲው አደረጃጀት ........ 4

የሰው ኃይል ........ 4

የዩኒቨርሲቲው የፋይናንስ ምንጭ ........ 4

**የኦዲቱ አላማ ........ 5**

**የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ........ 5**

**የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች ........ 5**

**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 6**

**የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቆሻሻ አወጋገድ የስራ ሂደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) ........ 6**

**የኦዲት ግኝቶች ........ 8**

ሀ/ ከዩኒቨርሲቲው የሚመነጩ የተለያዩ ቆሻሻዎችን ለመያዝ፣ ለማጓጓዝና ለማስወገድ የሚረዳ የአሰራር ሥርዐት መዘርጋቱና እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ ........ 8

*ቆሻሻን ለማስወገድ የተቀናጀ አሠራር ሥርዓት የተዘረጋ ስለመሆኑ፣ ........ 8*

*ቆሻሻን አወጋገድን የሚመለከቱ ተግባራትን ለሚያከናውኑ ሠራተኞች የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት በግልጽ ለይቶ የተቀመጠ እና እንዲያውቁት መደረጉን በተመለከተ ........ 8*

*የአከባቢ ዘላቂነት ዕቅድ (environmental sustainability Plan) ያዘጋጀ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ ........ 9*

ዩኒቨርሲቲው አካባቢያዊ ዘላቂነት ስተራቴጂክ ዕቅድ (environmental sustainability Strategy) ያዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ ........ 9

ዩኒቨርሲቲው የአካባቢያዊ ዘላቂነትን የማስረጽ (Environmental Sustainability Mainstreaming) ስራ በእቅድ በመያዝ ተግባራዊ ዐማድረጉን በተመለከተ ........ 10

ዩኒቨርሲቲው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ያዘጋጀና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ ........ 10

*በዩኒቨርሲቲው ከሚገኙ የተለያዩ የአካባቢ ዘላቂነት ክበባት ጋር በቅንጅት የሚሠራ መሆኑን በተመለከተ ........ 11*

*የቆሻሻ አወጋገድ ግንዛቤ እና ስልጠና መሰጠትን በተመለከተ ........ 11*

ቆሻሻን በማስወገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች የቆሻሻ አወጋገድ ዙሪያ ተገቢ ስልጠና መሰጠቱን በተመለከተ ........ 11

እንደ የቆሻሻው አይነት እና ባህሪ ቆሻሻን የማስወገድ ግንዛቤ ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎችና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ዘንድ እንዲኖር መደረጉን በተመለከተ ........ 12

ለ/ ከዩኒቨርሲቲ የተለያዩ ግቢዎች ከሚገኙ ቢሮዎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ላቦራቶሪዎች፣ የተማሪዎች መኝታ ቤቶች እና ምግብ ቤቶች የሚመነጩ የተለያዩ ቆሻሻዎችን ማስወገድን በተመለከተ፣ ........ 14

*ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸውን ቆሻሻዎች ለማስወገድ የሚያስፈልጉ ቁሰቀቁሶች እንዲሟሉ ማድረጉን በተመለከተ ........ 14*

እንደሚመነጩት የቆሻሻ አይነቶች ለማስወገጃ የሚያስፈልጉ ቁሰቀቁሶች እንዲሟሉ መደረጉን በተመለከተ ........ 14

ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ እና በማስወገድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች አስፈላጊው የመከላከያ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ ........ 14

የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በየኅዳናው ዳርና በሌሎች የተማሪዎችና ሠራተኞች ማዘውተሪያ ስፍራዎች የተቀመጡ መሆኑን በተመለከተ ........ 15

*ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸውን ቆሻሻዎች ጥቅም ላይ ለማዋል ሁኔታዎችን ያመቻቸ መሆኑን በተመለከተ ........ 15*

*የደረቅ ቆሻሻ ሲጓጓዝ እና ሲከማች እንዲሸፈን እና በወቅቱ እንዲነሳ ማድረጉን በተመለከተ ........ 16*

ቆሻሻዎች ሞልተው ሳይዝረከረኩ በየወቅቱ እነዲነሱ ማድረግን በተመለከተ ........ 16

ቆሻሻዎች የሚይዙ እና የሚጓጓዙባቸው ማጠራቀሚያዎች ሲጓጓዙ እንዲሸፈኑ ማድረጉን በተመለከተ .... **Error! Bookmark not defined.**

*የፍሳሽ ቆሻሻዎች አወጋገድ በተመለከ፤ ........ 17*

በቂና ተስማሚ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ሁኔታ እና ቦታዎችን ያመቻቸ እና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ማደረጉን በተመለከተ ........ 17

የፍሳሽ ቆሻሻዎችን መሬት ላይ እንዳይፈሱ ማድረጉን በተመለከተ ........ 19

*ከዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ስራ ክፍሎች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች ጉዳት እንዳያስከትሉ ጥረት የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ.......20*
የአደገኛ ቆሻሻን ከምንጩ ለመቀነስ የሚያደርገውን ጥረት በተመለከተ........................................................................ 20
ከማስተማሪያ የምርምር ቤተ-ሙከራዎችና ከክሊኒክ የሚወጡ አደገኛ የፍሳሽ ቆሻሻዎች ጉዳት እንዳያስከትሉ ጥረት የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ............................................................................................................................ 21
ከዩኒቨርሲቲው ጤና ተቋማት የሚመነጩ ስለታም የሆኑ አደገኛ ቆሻሻዎች አወጋገድን በተመለከተ.................................................... 21
*ከምግብ ቤቶች የሚመነጩትን ከምግብ ጋር የተያያዙ ቆሻሻዎች አወጋገድ በተመለከተ........................................................23*
*የደረቅ የቆሻሻ ማስወገኛ ቦታዎች የገተነቡ እና አስፈላጊውን ጥገና የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ.................................24*
*ከዩኒቨርሲቲው ደረቅ ቆሻሻን በማስወገድ ተግባር ላይ የተሰማራው አካል ህጋዊ ፈቃድ ያለው መሆኑን በተመለከተ................26*
*በዩኒቨርሲቲው በሚከረፉ ሽታ እንዳይኖር ማድረግን በተመለከተ.................................................................................27*
**የመደምደሚያ ሃሳቦች ........................................................................................................................ 28**
**የማሻሻያ ሃሳቦች.............................................................................................................................. 30**
**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት .................................................................................................................. 33**

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ቆሻሻ በሰው ልጆች እንቅስቃሴ የሚፈጠር ሲሆን፣ የሚፈጠረው የቆሻሻ አይነት በተለያዩ ምክንያቶች ሊለያይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ የማኅበረሰቡ የኑሮ ሁኔታ፣ ሥራ፣ የአካባቢ አየር ፀባይ እና የአመጋገብ ልምድ ከምክንያቶቹ ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች የሚፈጠረውን የቆሻሻ ዓይነትና መጠን የሚወስኑ ሲሆን፣ እንደየዓይነታቸው የእያንዳንዱ ቆሻሻ የተለየ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ሥርዓት ይፈልጋል፡፡ በአብዛኛው በማደግ ላይ ባሉ አገሮች የሚፈጠሩ ቆሻሻዎች ተፈጥሮአዊና በቀላሉ ለመበስበስ የተጋለጡ ስለሆኑ በእነዚህ አገሮች የቆሻሻ አያያዝ፣አጓጓዝና አወጋገድ ሥርዓት በቆሻሻ መሰብሰብ ሂደት ላይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

2. ቆሻሻ በአግባቡ ካልተያዘ በሰው ልጆች፣ በአካባቢ እና እንስሳት ደህንነት ላይ ከፍተኛ አደጋ ያስከትላል፡፡ በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮገራም በቆሻሻ የሚመጣ ብክለት በዓለም ላይ ካሉ የአካባቢ ጉዳዩች አንዱ እና ዋነኛው መሆኑ ታምኖበታል፡፡

3. በሀገራችን ብዙ ህዝብ ተሰብስቦ ከሚኖርባቸው እና ከሚሠራባቸው ቦታዎች በሚመደቡት ዩኒቨርሲቲዎች የቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሂደት ላይ ከሚታየው አነስተኛ ትኩረት አንፃር ችግሩ በጉልህ ይታያል፡፡ በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ለቆሻሻ አያያዝና አጠባበቅ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር ከዩኒቨርሲቲዎች የቅበላ አቅም ማደግ ጋር ተያይዞ የሚፈጠረው ቆሻሻ በዓይነትም ሆነ በብዛት እየጨመረ የሚሄድ መሆኑ ለጉዳዩ የተለየ ትኩረት እንዲሰጠው ያስገድዳል፡፡ በመሆኑም የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት በአዲስ አባበ ዩኒቨርሲቲ የቆሻሻ አያያዝ አጓጓዝና አወጋገድ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

4. የመጀመሪያው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በ1950 ዓ/ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ስም የተመሰረተ ሲሆን፣ ይኸው ተቋም በ1962 ዓ/ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በመባል ተሰይሞ የነበረ እና በአሁኑ ወቅት መጠሪያው የሆነውን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስያሜን ያገኘው በ1975 ዓ/ም እንደሆነ ከታሪክ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ይህ ዩኒቨርስቲ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች የመጀመሪያ፣ የሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ መርሐ ግብሮችን እየሰጠ ይገኛል፡፡ መንግስት በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ያለውን የከፍተኛ ትምህርት አቅም ለማሳደግ ባለው ራዕይ መሠረት ይህ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ መርሐ ግብሮችን በተለያዩ ኮሌጆች፣ ፋክልቲዎች፣ ትምህርት ቤቶችና

ኢንስቲትዩቶች በማስፋፋት  የጥናትና ምርምር ሥራዎች በስፋት እንዲያከናውን መደረጉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

5. በመንግስት በወጣው የአከባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ላይ ማንኛውም ድርጅትም ሆነ ግለሰብ በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ረገድ ቆሻሻው እንዳይመነጭ ከምንጩ የመከላከል ከመነጨ በኃላ አግባብነት ባለው እና አመቺ በሆኑ ዘዴዎች ሊወገዱ ውይም ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ እንዳለበት ተጠቅሷል፡፡

6. በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የወረቀት አጠቃቀም መጠን በጣም ከፍተኛ መሆኑ እና ከዚህም ውስጥ የተማሪዎች ድርሻ የጎላ እንደሆነ በዚህ ዙሪያ የተደረገ ጥናት ያሳያል፡፡ ከወረቀት በተጨማሪ የምግብ ቤቶች፣ የመጸዳጃ ቤቶች ከህክምና ተቋማትና ምርምር ላብራቶሪዎች የተለያዩ ባህሪ ያላቸው የደረቅ የፍሳሽና አደገኛ ቆሻሻዎች ይመነጫሉ፡፡

7. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሃገሪቱ ቀደምትና ትልቁ እንደመሆኑ መጠን ለዕይታ ማራኪ፣ አካባቢው ለኑሮና ለሥራ የተመቸና በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓቱ ለሌሎች ተቋማት አርዓያ መሆን የሚጠበቅበት ተቋም ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከሌሎች ዓለምአቀፍ ተቋማት ጋር ባለው ቅርበት ለእድገትና ለመስፋፋት ያለው አቅም ከፍተኛ በመሆኑ፣ ያለው የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ሥርዓት ከድርጅታዊ አወቃቀሩ ተያይዞ እንዲሻሻል ማድረጉ የቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገዱ በተሻለ ሁኔታ እንዲከናወን ለማድረግ ያስችላል፡፡

# ዩኒቨርስቲው የተቋቋመበት ዓላማ

8. ዩኒቨርሲቲው የተቋቋመበት ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ሲሆኑ፣ እነሱም፡-

- ✓ እውቀትን ማዳበር፣ ማስፋፋትና ማስተላለፍ፥ ከዘር፣ ከብሔር፣ ከጾታ፣ ከሃይማኖትና ከመሳሰሉት ተጽዕኖዎች ነጻ የሆነ በመከባበር፣ መተማመን፣ በመተሳሰብ እና በመቻቻል ላይ የተመሠረተና ሁለንተናዊ ስብዕናን የሚያበለጽግና የሰው ልጅ ክቡርነትን የሚያጠናክር ትምህርት መስጠት፤
- ✓ የሥራ ክቡርነትንና የህብረተሰብ ብልጽግናን የሚያራምድ አስተሳሰብ እንዲሰርጽ ማድረግ፥ የኢትዮጵያን ህዝብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በሥነ ጥበባትና በልዩ በልዩ ሙያዎች የሰለጠነ፣ ኅብረተሰብን በሚገባ ሊያገለግሉ የሚችሉ ሰዎች ማፍራት እንዲሁም

- ✓ በልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች በገለልተኝነት እንዲሁም ከስሜትና ከማንኛውም ተፅዕኖ ነጻ የሆነ ጥናትና ምርምር ማካሄድና ጠቃሚ ውጤቶችን ማሰራጨት፤

የሚሉት ናቸው፡፡

9. በሀገራችን ማንም ሰው ሊከተላቸው ይገባል ተብሎ ከወጡ አዋጆች መካከል የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/2002 መሠረት፤

   - ✓ ማንም ሰው ተገቢውን የአካባቢ ደረጃ በመተላለፍ አካባቢን ሊበክል ወይም በሌላ ሰው በኩል እንዲበከል ሊያደርግ አይፈቀድለትም፣
   - ✓ ሕግ በመተላለፍ ማንኛውንም በካይ ነገር ወደ አካባቢ በሚለቅ ሰው ላይ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት አስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ ዕርምጃ መውሰድ ይችላል፣
   - ✓ ብክለትን ወይም ሌላ አካባቢያዊ ጉዳትን ሊያስከትል በሚችል የተግባር መስክ የተሠማራ ማንም ሰው ቆሻሻ ማመንጨትን ለማስወገድ ወይም ወደተፈላጊው መጠን ለመቀነስ በባለስልጣኑ ወይም በሚመለከተው የአካባቢ መ/ቤት ትዕዛዝ መሰረት በተገቢ ቴክኖሎጂና ቢቻልም ቆሻሻን መልሶ በጥቅም ላይ ለማዋል በሚያስችሉ ዘዴዎች መጠቀም አለበት፣
   - ✓ ብክለትን ያደረሰ ማንኛውም ሰው ባለስልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መ/ቤት በሚወስነው ሁኔታና የጊዜ ገደብ መሠረት አካባቢውን ከብክላ ማጽዳት ወይም ለማጽጃ የወጣውን ወጪ መሸፈን አለበት፡፡

10. ዩኒቨርስቲው በዋነኛነት የተቋቋመው ሳይንሳዊ ዕውቀትን በተለያዩ ምርምሮች በማጠናከር ማስፋፋትና ለሀገሪቱ ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት የጎላ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ዜጎችን ማፍራት ቢሆንም፣ ለዚህ አዋጅ ተገዢ በመሆኑ የዩኒቨርስቲውን ማህበረሰብ የመኖሪያና የስራ አከባቢ ከብክነት የጸዳ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡በተጨማሪም በአከባቢ ጥበቃ ረገድ በቲዎሪ እየሰጠ ያለውን ትምህርት በተግባርም በማሳየት ለሌሎች ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ለሌላው ማህበረሰብ አርዓያ መሆን ይገባዋል፡፡

# የዩኒቨርሲቲው ስልጣንና ተግባር

11. በአዋጅ ቁጥር 2/1983 አንቀጽ 4/2 እና በአዋጅ ቁጥር 41/1985 አንቀጽ 12/8 መሠረት በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 113/1985 ዩኒቨርሲቲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡፡

   - ✓ ፋክልቲዎች ኮሌጆችና ሌሎች የትምህርትና የምርምር ተቋማት ማቋቋምና ማካሄድ፤
   - ✓ የቅድመ ምረቃና የድህረ ምረቃ ፕሮግራም መቀየስና ስራ ላይ ማዋል፤

- ✓ የምስክር ወረቀት ዲፕሎማና ዲግሪ እንዲሁም ለከፍተኛ ውጤትና አስተዋፅኦ ሜዳሊያ ሽልማትና ማፅረግ መስጠት፣
- ✓ ሴሚናሮች ወርክ ሾፖችና ሲምፖዝየሞችን ማዘጋጀትና ማካሄድ፣
- ✓ በሌሎች አገሮች ከሚገኙ አቻ ዩኒቨርስቲዎች የምርምር ተቋማትና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ጋር ግንኙነት መመስረት፤
- ✓ የትምህርት መፅሄቶችና ጋዜጦች ማቋቋምና ማስራጨት፤
- ✓ ዓላማውን የሚያራምዱ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፤

# የዩኒቨርሲቲው አደረጃጀት

12. በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 በተደነገገው መሠረት ዩኒቨርስቲው በአንድ ፕሬዚደንት የሚመራ እና ለፕሬዝዳንቱ ተጠሪ የሆኑ አራት ም/ፕሬዚደንቶች እና አንድ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር ያሉት ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርስቲው በ10 ኮሌጆች፤ 3 ትምህርትና ምርምርን አጣምረው በያዙ ኢንስቲትዮቶች እና በ6 የምርምር ኢንስቲትዮቶች ተደራጅቷል፡፡ ዩኒቨርስቲው 63 የቅድመ ምረቃ፤ 293 የድህረ ምረቃ (72 የዶክትሬት፤ 221 የማስተርስ) መርሐ ግብሮች አሉት፡፡ በእነዚህ አደረጃጀት ውስጥ 55 የትምህርት ክፍሎች፤ 12 ማዕከላት፤ 9 ት/ቤቶች፤ 2 የማስተማሪያ ሆስፒታሎች ተካተዋል፡፡

# የሰው ኃይል

13. በዩኒቨርሲቲው እስከ ሰኔ 30 /2004 ዓ.ም 3160 ወንድ እና 2351 ሴት በድምሩ 5511 ቋሚ እና 1296 ወንድ እና 1554 ሴት በድምሩ 2850 ኮንትራት በጠቅላላ 8361 ሠራተኞች እንዳሉት ታውቋል፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ ፒኤችዲ 586 ፣ ማስተርስ ዲግሪ 752፣ የመጀመሪያ ደግሪ 853 ፣አድቫንስድ ዲፐሎማ 762፣ ከዲፐሎማ በታች 1151 ናቸው፡፡

# የዩኒቨርሲቲው የፋይናንስ ምንጭ

14. ዩኒቨርሲቲው ተልዕኮውን ለማሳካት ከመንግስት ከሚመደብለት መደበኛ በጀት፣ ከሚሰበስባቸው የአገልግሎት ክፍያ እንዲሁም ከሌሎች ምንጮች ከሚገኙ ገቢዎች ስራውን እንደሚያከናውን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት በ2002፣ በ2003 እና በ2004 በጀት ዓመታት እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 478.0፣ 266.5 እና 643.0 ሚሊዮን ብር ከመንግሥት የተመደበለት ሲሆን፣ ከዚህ ወስጥ ሥራ ላይ የዋለው እንደ ቅደም

ተከተሉ 197.4 ፣ 244.5 እና 588.0 ሚሊዮን ብር ሲሆን፣ ይህም በመቶኛ ሲገለጽ 42 %፣ 91.74% እና 91.44% መሆኑ ታውቋል፡፡

# የኦዲቱ አላማ

15.የኦዲቱ ዓላማ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ሥርዓት መዘርጋቱን እና ሥራው ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በብቃትና በስኬታማነት ጉዳት በማያስከትልና ዘላቂነትን በጠበቀ መንገድ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ ሲሆን፤ ይህን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት፣ ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

# የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

16.ከላይ በተለየው የኦዲቱ ዓላማ ስር ሁለት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ የተለዩ ሲሆን፣ በሁለተኛው የትኩረት አቅጣጫ ስር ሶስት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡

1. ከዩኒቨርሲቲው የሚመነጩ ደረቅ፣ ፍሳሽ እና አደገኛ ቆሻሻዎችን ለመያዝ፣ ለማጓጓዝና ለማስወገድ ተገቢው የአሠራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፣
2. ዩኒቨርሲቲው ከቢሮዎች፣ ከጤና ጣቢያዎች፣ ላቦራቶሪዎች፣ የተማሪዎች መኝታ ቤት እና ከምግብ ቤቶች የሚመነጩ ደረቅ እና ፈሳሽ እንዲሁም አደገኛ ቆሻሻዎችን የመያዝ፣ የማጓጓዝና የማስወገድ ተግባር ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ፣ በብቃት እና በስኬታማነት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም፣
   1. የደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ ማጓጓዝ እና አወጋገድ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ፣ በብቃት እና በስኬታማነት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም፣
   2. የፍሳሽ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ ማጓጓዝ እና አወጋገድ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ፣ በብቃት እና በስኬታማነት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም፣
   3. የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ ማጓጓዝ እና አወጋገድ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ፣ በብቃት እና በስኬታማነት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም፣

ናቸው፡፡

# የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች

17.በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሁለት ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን እና ሶስት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 28 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶችን

ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት በሀገር አቀፍ የወጡ የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ አዋጆችና እና መመሪያዎች፣ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ እና የመልካም ስራ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡በተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስራ ሃላፊዎች አስተያየት ሰጥተውበታል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖረት ጋር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

# የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

18. ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ ውስጥ ሲሆን፣ ከጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ከተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ፣ ከአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ከቢዝነስና አኮኖሚክስ ኮሌጅ፣ ከንግድ ስራ ኮሌጅ፣ ከአርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት፣ ከአቃቂ ሀገር ልማት ፕሮጀክት ኮሌጅና ከደብረ ዘይት እንስሳትና ግብርና ኮሌጅ የስራ ሃላፊዎች ጋር የኦዲት ቡድኑ ቃለ-መጠይቅ በማድረግ፣ በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጡ መረጃዎች በመከለስና በአከባቢ ጥበቃ ዙሪያ በተለይም በቆሻሻ አሰባሰብ አያያዝ እና አወጋገድ ዙሪያ ካሉ ከመልካም ተሞከሮዎች መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ሶስት የበጀት ዓመታት ከ2002 እስከ 2004 ዓ.ም ባለው ጊዜ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቆሻሻ አያያዝ አጓጓዝና አወጋገድ በተመለከተ የተከናወኑ ስራዎች ላይ ነው፡፡

# የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቆሻሻ አወጋገድ የስራ ሂደት መግለጫ (process description)[1]

19. የደረቅ፣ የፈሳሽ እና የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ አሰባሰብ፣ አጓጓዝ እና አወጋገድ ሥራዎች ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ፣ የደረቅ፣ የፈሳሽ እና የአደገኛ ቆሻሻ ከምንጩ እስከ አወጋገዱ ሰንሰለታዊ በሆነ መንገድ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ የቆሻሻዎች አሰባሰብ፣ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ እንደ ቆሻሻዎቹ አይነት እና ባህርይ የሚለያይ ሲሆን፣ ከምንጫቸው ጀምሮ በአይነታቸው በመለየት ሊቀመጡና ሥራው በሚመለከታቸው አካላት ተሰበሰበው ወደሚከማቹበት ቦታ ተጓጉዘው ይከማቻሉ፡፡ የፍሳሽ ቆሻሻ ከሆኑ በተዘጋጀላቸው የፍሳሽ መስመር በመተላለፍ ለማስወገድ ወተዘጋጀላቸው አካባቢ እንዲፈሱ ይደረጋል፡፡

20. ከዩኒቨርሲቲው ሁሉም አይነት ቆሻሻዎች ማለትም ደረቅ፣ ፈሳሽ አና አደገኛ ቆሻሻዎች የሚመነጩ ሲሆን፣ እነዚህ ቆሻሻዎች ከተማሪዎች መኝታ ቤት፣ የመመገቢያ ቦታዎች፣

1

ከሠራተኛ ቢሮዎች፣ ከክሊኒኮች/ሆስፖታሎች፣ ከምርምር ላቦራቶሪዎች እንዲሁም ከግቢ የቅጠላ ቅጠል ጥራጊ እና በየቦታው ከሚጣሉ ውዳቂዎች ይመነጫሉ፡፡

21. በዩኒቨርሲቲው የሚመነጩ ቆሻሻዎች በተቻለው መጠን ከምንጫቸው መጠናቸው እንዲቀንስ፣ እንደገና መልሶ በቀጥታ ለመጠቀም ወይም ግብዐት በመጨመር (recycle) በማድረግ ለሌላ አገግሎት እንዲውሉ ወይም ለሃይል ምንጭነት፣ ለማዳበሪያና በመዋል ጥቅም እንዲሰጡ በማድረግ እንደአመቺነቱ ይወገዳሉ፡፡

22. የቆሻሻዎች አወጋገድ እንደ ባህርያቸው የሚለያየይ ሲሆን፣ በመጀመሪያ ከምንጫቸው በቀጥታ ጥቅም ላይ የሚውሉ፣ የተወሰነ ለውጥ ተደርጎባቸው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ፣ ወይም ለኃይል ምንጭነት እና ለማዳበሪያ አገግሎት የሚሆኑት ተለይተው እንዲሰበሰቡ የደረጋል፡፡ ተገቢውን የመከለካያ ልብስ፣ ቆብ እና የእጅ ጓንት ባደረጉ ሠራተኞች ቆሻሻዎች እንዲጓጓዙ የሚደረግ ሲሆን፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥቅም ላይ የማይውሉት ለብቻ ተሰብስበው እና በጥንቃቄ ተጓጉዘው በማቃጠል ወይም በመቅበር እንዲወገዱ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን በማስተላለፍ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

23. በተለያየ መንገድ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚገባቸው ቆሻሻዎች ማለትም የመጸዳጃ ቤቶች ፈሳሽ፣ ተረፈ፣ ምግቦች ወዘተ ለዚህ በተዘጋጁ ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ ለባዮጋዝ ወይም ለማዳበሪያ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በቀጥታ ያመነጫቸው አካል ሊጠቀምባቸው የማይችል ከሆነ ለመጠቀም ለሚችሉ ሶስተኛ ወገኖች እንዲተላለፉ በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይችላል፡፡ የቆሻሻው አመንጪ በራሱ የሚያስወግዳቸው ቆሻሻዎችን በከተማው አስተዳደር በኩል ባለው የማስወገጃ ሥራዓት መሠረት እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

24. ከዩኒቨርሲቲው የምርምር ቤተሙከራዎች እና ከክሊኒኮች የሚመነጩ አደገኛ ቆሻሻዎች በከተማው አስተዳደር የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር እንዲገቡ ሊደረግ ይህ አይነት ግንኙነት ከከተማው የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ጋር የማይገናኙ ከሆነ ከመወገዳቸው በፊት በያዙት ጎጂ ንጥረ ነገር ጉዳት እንዳያስከትሉ በማከም (by treat) ይወገዳሉ፡፡ ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶች እና ኬሚካሎችን እንደ አደገኝነታቸው ደረጃ በመቅበር ወይም ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትሉ እና የተለየ ጥንቃቄ የሚጠይቁ ከሆነ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት የዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## ሀ/ ከዩኒቨርሲቲው የሚመነጩ የተለያዩ ቆሻሻዎችን ለመያዝ፣ ለማጓጓዝና ለማስወገድ የሚረዳ የአሰራር ሥርዐት መዘርጋቱና እና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

### ቆሻሻን ለማስወገድ የተቀናጀ አሠራር ሥርዓት የተዘረጋ ስለመሆኑ፣

25.ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል፣ ጉዳት እንዳያመጣ ለማምከንና ለማስወገድ የሚያስችለውን የተቀናጀ የአሰራር ስርዐት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ለዚህም መመሪያ ሊያወጣና ተገቢውን ስልጠና መስጠት ይኖርበታል፡፡

26.ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸውን ደረቅ፣ ፈሳሽና አደገኛ ቆሻሻዎች ለመሰብሰብ፣ ለማጓጓዝ፣ እንደ አግባብነቱ ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማስወገድ የሚያስችለውን ወጥ የሆነ የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝ የአሰራር ስርአት አልዘረጋም፡፡

27.ስለ ሁኔታው የዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻ ለመሰብሰብ፣ ለማጓጓዝ፣ እንደ አግባብነቱም ጥቅም ላይ ለማዋልና ለማምከን የሚያስችለው አሰራር በቂ ትኩረት ተሰጥቶ አለመስራቱና ክትትል አለማድረጉን በመጥቀስ ወጥ የሆነ የአሰራር ስርአት ያልዘረጋ በመሆኑ ስራው በተለምዶ ብቻ የሚከናወን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

28.ይህ ሥርዓት አለመዘርጋቱ ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል፣ጉዳት እንዳያመጣ ለማምከንና ለማስወገድ የሚያስችለውን የተቀናጀ የአሰራር ስርዐት ባለመዘርጋቱና መመሪያ ባለማውጣቱ ቆሻሻን በአይነትና በባህሪ ለይቶ የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣የማጓጓዝ፣ የማስወገድና መልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ስራ በተፈለገው መጠን እንዳይከናወን አድርጓል፡፡

### ቆሻሻን አወጋገድን የሚመለከቱ ተግባራትን ለሚያከናውኑ ሠራተኞች የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት በግልጽ ለይቶ የተቀመጠ እና እንዲያውቁት መደረጉን በተመለከተ

29.ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ፣ አያያዝ አጓጓዝና አወጋገድ ሰንሰለት ስራዎችን የሚመለከቱ ተግባራትን ለሚያከናውኑ ሠራተኞች የስራ ደርሻ እና ሃላፊነት በግልጽ ለይቶ

ሊያስቀምጥ እና የሚያከናውኑት ተግባራት በግልጽ ተለይቶ በጽሁፍ እንዲደርሳቸው ሊደረግ ይገባል፡፡ ሆኖም ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን የሚመለከቱ ተግባራት ለሚያከናውኑ ሰራተኞች የስራ ድርሻ እና ሃላፊነታቸውን በግልጽ ለይቶ አላስቀመጠም፤ ሥራው የሚመለከታቸው ሰራተኞችም ዝርዝር ሥራ በጽሁፍ እንዲደረሳቸው አልተደረገም፡፡

30. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በዩኒቨርስቲው ለቆሻሻ አያያዝ፣ አንጓዝና አወጋገድ የአሰራር ስርአት ያልተዘረጋ፤ ጉዳዩን የዕለተ ተዕለት ስራው አድርጎ የሚከታተል የስራ ክፍል በግልጽ የሌለ በመሆኑ፤ የስራ ድርሻ እና ሃላፊነት በግልጽ ተለይቶ ያልተቀመጠ እና ግዴታቸው በጽሁፍ እንዲደርሳቸው ያልተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

31. ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን የማስወገድ ተግባር የሚያከናውን አካል ባለመቋቋሙ እና ይህንን ተግባር ለሚያከናውኑ ሠራተኞች የሚያከናውኑት ተግባር በጽሁፍ እንዲደርሳቸው አለመደረጉ የቆሻሻ ማስወገድ ተግባር ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ፣ በብቃት እና በውጤታማነት እንዳይከናወን ከማድረጉም በላይ ሠራተኞች በቆሻሻ ማስወገዱ ረገድ የሚኖራቸውን ኃላፊነት በመገንዘብ ስራቸውን እንዳያከናውኑ ያደርጋል፡፡

## የአከባቢ ዘላቂነት ስልት (environmental sustainability Strategy) ያዘጋጀ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ

### *ዩኒቨርሲቲው አካባቢያዊ ዘላቂነት ስተራቴጂክ ዕቅድ (environmental sustainability Strategy) ያዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ*

32. ዩኒቨርሲቲው የአካባቢ ዘላቂነት ስትራቴጂክ (environmental sustainability Strategy) ዕቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ ሆኖም የአከባቢ ዘላቂነት ስትራቴጂ ዕቅድ በዩኒቨርስቲው ደረጃ አልተዘጋጀም፡፡

33. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ከላይ እንደተጠቀሰው በዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አወጋገድ ሥርአት ባለመዘርጋቱ የአከባቢያዊ ቀጣይነት ስትራቴጂክ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

34. ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ የአከባቢ ዘላቂነት ልማት ስትራቴጂክ እቅድ ባለመኖሩ በዩኒቨርሲቲውና በሀገር አቀፍ ደረጃ አከባቢያዊ ዘላቂነት ላይ ጎጂ ተጽኖ ይፈጥራል፡፡

***ዩኒቨርሲቲው የአካባቢያዊ ዘላቂነትን የማስረጽ (Environmental Sustainability Mainstreaming) ስራ በእቅድ በመያዝ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ***

35. ዩኒቨርሲቲው የአካባቢያዊ ዘላቂነት (Environmental Sustainability) አመለካከትን የማስረጽ እና የማነሳሳት አካል የሆነው የሜይንስተሪሚንግ ስራ በአደረጃጀቱ ውስጥ ተካተው እንዲታቀዱና እንዲተገበሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ሆኖም ዩኒቨርሲቲው የአካባቢ እና ዘላቂነት (Environmental Sustainability) በተመለከተ በቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ዙሪያ የሜይንስትሪሚንግ ስራ በእቅዱ በማካተት ተግባራዊ አላደረገም፡፡

36. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አወጋገድ የአሰራር ስርዐት ያልዘረጋ በመሆኑ የአካባቢ ዘላቂነትን ለማረጋገጥ የሜይንስትርሚንግ ስራ በእቅዱ ውስጥ ተካቶ አለመሠራቱን ገልጸዋል፡፡

37. ዩኒቨርሲቲው የአከባቢ እና ዘላቂነት ሜይንስትሬሚንግ ስራ በእቅዱ አካቶ ተግባራዊ ባለማድረጉ (enviromental sustainability) የአካባቢ ዘላቂነትን የባለቤትነት ስሜት በዩኒቨርሲቲው ማኀበረሰብ እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡

***ዩኒቨርሲቲው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ያዘጋጀና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ***

38. ዩኒቨርሲቲው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ፣ በአመት ምን ያህል ቆሻሻ ከዩኒቨርሲቲው እንደሚያመነጭ እና በምን አይነት መንገድ መሰብሰብ፣ መያዝ፣ መጓጓዝና መወወገድ እንዳለበት የሚያሳይ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

39. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት የደረቅ ቆሻሻ ዕቅድ ያልተዘጋጀና ተግባራዊ ያልሆነ መሆኑ ታውቋል፡፡

40. የዩኒቨርሲቲው የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አወጋገድ አሰራር ስርዐት ያልተዘረጋ በመሆኑ አመታዊ ዕቅድም ሆነ ሌሎች ዕቅዶች በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ እንዳልተሠራ እና ነገር ግን ስራው በተለምዶ እንደሚከናወን ገልጸዋል፡፡

41. ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን በአግባቡ ለመሰብሰብ፣ ለማጓጓዝና ለማስወገድ እቅድ ባለመዘጋጀቱ የሚመነጨውን እና ሊወገድ የሚገባውን የቆሻሻ መጠን በመገመት እና በመዘጋጀት የተሻለ የቆሻሻ አወጋገድ ክንውን ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዳይከናወን ያደርገዋል፡፡

## በዩኒቨርሲቲው ከሚገኙ የተለያዩ የአካባቢ ዘላቂነት ክበባት ጋር በቅንጅት የሚሠራ መሆኑን በተመለከተ

42. ዩኒቨርሲቲው በተማሪዎች ከሚመሩ የአካባቢ ዘላቂነት ክበባት ጋር በትብብር የሚሰራበት ሥርዓት በመዘርጋት በሁሉም የአካባቢ ጉዳዮች ቀጣይነት ያላቸው ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡

43. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደታየው፣ በዩኒቨርሲቲው የአካባቢ ዘላቂነት ክበባት የተቋቋሙ ቢሆንም፣ ለክበቦች ድጋፍ ማድረግና በጋራ ተቀናጅቶ በሁሉም የአካባቢ ጉዳዮች ላይ ቀጣይነት ያላቸው ስራዎች ላይ የማሳተፍ ስራ አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

44. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በአካባቢ ጉዳይ ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች የሚሰራበት ሁኔታ መኖሩን፤ ነገር ግን የአካባቢ ዘላቂነትን በተመለከተ በዩንቨርሲቲው በትምህርት ክፍሎች መካከል ተናቦ ያለመስራትና ከክበባት ጋር በትብብር የሚሰራበት ሁኔታ አነስተኛ መሆኑ፤ እንዲሁም በትምህርት ክፍሎች መካከል ለየትኛው ትኩረት መሰጥት እንዳለበት የሚያመላክት ግልጽ የሆነ አካሄድ አለመኖሩ ገልጸዋል፡፡

45. ዩኒቨርሲቲው በተማሪዎች ለሚመሩ የአካባቢ ዘላቂነት ክበባት ተገቢውን ድጋፍ አለማድረጉና በቅንጅት የሚሰራበት ሁኔታዎች ባለመመቻቸቱ አካባቢን በመጠበቅ በተለይም ቆሻሻን በማስወገዱ ረገድ ቀጣይነት ያላቸው ተግባራትን ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉበት ደረጃ ለመተግበር እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## የቆሻሻ አወጋገድ ግንዛቤ እና ስልጠና መስጠትን በተመለከተ

### *ቆሻሻን በማስወገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሠራተኞች የቆሻሻ አወጋገድ ዙሪያ ተገቢ ስልጠና መሰጠቱን በተመለከተ*

46. በቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች የቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ተገቢው ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡

47. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ቆሻሻን በመሰብሰብ በማጓጓዝና በማስወገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች በአከባቢውም ሆነ በራሳቸው ላይ ጉዳት በማያስከትል እና አመቺ በሆነ መልኩ ቆሻሻን መሰብሰብ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝና ማስወገድ እንዳለባቸው የሚረዳቸው ተገቢው ስልጠና አለመሰጠቱ ታውቋል፡፡

48. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩ የዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ግቢዎች የስራ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች በእቅድ ውስጥ በማካተት የረጅምና አጭር ጊዜ ስልጠና ለሰራተኞቹ ሊሰጥ ቢገባም፣ የቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ስልጠና በእቅድ ተይዞ እንደማይሰጥ፤ ነገር ግን ሰራተኛው ሲቀጠር ስለሚሰራው ስራ አብሮት ከሚሰራው ሰራተኛ በማየት በልምድ የሚሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

49. በሌላ በኩል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የበላይ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አወጋገድ ላይ በቀጥታ ያተኮረ ስልጠና ባይሆንም በተወሰነ መልኩ ስልጠና እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡

50. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በቆሻሻ አያያዝ አጓጓዝና አወጋገድ ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱ የሚገልጽ መረጃ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ተገቢው ስልጠና ባለመሰጠቱ በቆሻሻ አወጋገድ ሂደት ላይ ሠራተኞች የተሻለ ብቃት እንዳይኖራቸውና የማስወገድ ተግባሩንም ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዳያከናውኑ ያደርጋል፡፡

***እንደ የቆሻሻው አይነት እና ባህሪ ቆሻሻን የማስወገድ ግንዛቤ በሰራተኞች፣ በተማሪዎችና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ዘንድ እንዲኖር መደረጉን በተመለከተ***

51. ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማለትም እንደ ቆሻሻው አይነት እና ባህሪ በመለየት የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣ የማጓጓዝና የማስወገድ ስራን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲኖርና ስራው እንዲከናወን ሊያደርግ ይገባል፡፡

52. ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድን በተመለከተ በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን ተከትሎ ማለትም ደረቅ፣ ፈሳሽ እና አደገኛ የሆኑትን ቆሻሻዎች በአይነትና በባህሪ በመለየት ማሰባሰብ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ እና ማስወገድን በተመለከተ ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎችና ለባለድርሻ አካላት ዘንድ ግንዛቤ እንዲኖር እና ይህን የቆሻሻ አወጋገድ መሠረት በማድረግ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት ሁኔታ እንዲፈጠር አላደረገም፡፡

53. የኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት፣ የጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ አራት ኪሎ ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንሲቲትዩት፣ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ፣ የንግድ ስራ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት፣ አቃቂ የሀገር ልማት እና ደብረ-ዘይት የእንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ ቆሻሻ

ደረቅ፣ፈሳሽና አደገኛ ቆሻሻዎችን በአይነት እንዲሁም በባህሪ አደገኛ የሆኑትን፣ በመለየት የማያስወግዱ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

54. በዩኒቨርሲቲው ስር ከሚገኙ ኮሌጆች መካከል በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩ ግቢዎች የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ስለ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በተለያዩ ጊዜያት ስልጠና በተወሰኑት የዩኒቨርስቲው ክፍሎች ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚሰጥ ቢሆንም ወጥ በሆነ መልኩ እየተከናወነ አለመሆኑን፤ በጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለሚመለከታቸው ባለድረሻ አካላት የእንፌክሽን መከላከል “infection prevention” በሚለው ላይ ስልጠና ተካቶ እንደሚሰጥ፤ በተማሪ ቅበላ ወቅትም በየተቋማቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እንደሚሰሩ፤ በተጨማሪም ቆሻሻ ለሚያስወግዱ ቡድኖች ወጥነት የሌለው ቢሆንም፣ ቆሻሻ እንዴት መያዝ እንዳለባቸው ስልጠናዎች የሚሰጡ መሆንና ነገር ግን የሚሰበሰቡ ቆሻሻዎችን የሚያስወግዱ ሰራተኞችን በወቅቱ እንዲያነሱ ክትትል በማድረጉ ረገድ ድክመቶች እንዳሉ ገልጸዋል፡፡

55. በሌላ በኩል ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን በአይነትና በባህሪ በመለየት፣ የመያዝ ፣የማጓጓዝና የማስወገድ ስራ የቆሻሻ አወጋገድ ስርዐትን ያልተከተለና በተለምዶ የሚሰራ እንደሆነ፤ ነገር ግን የሚፈለገውንና የታሰበውን ያህል ባይሆንም በባህሪና በአይነት መለየት ስራ በተወሰነ ደረጃ የሚከናወን መሆኑን፤ በዩኒቨርሲቲው ስለ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ለባለ ድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በቂ በሆነ መልኩ ባይሰራም በተወሰነ መልኩ በአመቱ መጀመሪያ ተማሪዎች ተመድበው ወደ ዩኒቨርስቲው በሚመጡበት ወቅት ስለ ንጽህና አጠባበቅ ስለአመጋገባቸውና በአጠቃላይ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

56. ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻዎችን በአይነትና በባህሪ ተለይቶ፣ የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣የማጓጓዝና የማስወገድ ስራ ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና ይህንንም ተከትለው እንዲያከናውኑ ባለመደረጉ ቆሻሻን በአይነትና በባህሪ ለይቶ የመሰብሰብ፣ የማጓጓዝ እና የማስወገድ ስራ በተገቢው መልኩ እንዳይከናወን አድርጓል፡፡

## ለ/ በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ግቢዎች ከሚገኙ ቢሮዎች፣ ክሊኒኮች፣ ላቦራቶሪዎች፣ የተማሪዎች መኝታ ቤቶች እና ምግብ ቤቶች የሚመነጩ የተለያዩ ቆሻሻዎችን ማስወገድን በተመለከተ፣

### ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸውን ቆሻሻዎች ለማስወገድ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ማድረጉን በተመለከተ

***እንደሚመነጩት የቆሻሻ አይነቶች ለማስወገጃ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ መደረጉን በተመለከተ***

57.እንደሚመነጩት የቆሻሻ አይነቶች ለማጠራቀሚያ፣ ለማጓጓዣ እና ማስወገጃ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ሊሟሉ ይገባል፡፡

58.ይሁን እንጂ በኦዲቱ በዩኒቨርሲቲው እንደሚመነጩ ቆሻሻ አይነቶች ለማጠራቀሚያ፣ ለማጓጓዣና ለማስወገጃ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የተሟሉ ሆነው አልተገኙም፡፡

59.የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ ካያቸው የዩኒቨርሲቲው ቅርንጫፎች የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ፣የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንሲትትዩት፣ አቃቂ የሀገር ልማት ፕሮጀክትና ደብረዘይት እንስሳትና ግብረና ኮሌጅ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ/ማከማቻ ገንዳ የላቸውም፡፡

***ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ እና በማስወገድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች አስፈላጊው የመከላከያ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ የተደረገ መሆኑን በተመለከተ***

60.የደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ እና በማስወገድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞ አስፈላጊው የመከላከያ ቁሳቁሶች እንዲሟላላቸው ሊደረግ ይገባል፡፡

61. ሆኖም በቆሻሻ አወጋገድ ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች አስፈላጊው የመከላከያ ቁሳቁስ እንደሚቀርብ የተገለጸ ቢሆንም የኦዲት ቡድኑ በአካል በጎበኘበት ወቅት ሠራተኞች አደገኛ ቆሻሻ በሚያስወግዱበት ወቅት የመከላከያ ቀሳቁስ በተሟላ መልኩ የማይጠቀሙ መሆኑን የተመለከተ እና ሰራተኞቹ ተጠይቀው የተሟላ ቁሳቁስ እንዳልተሰጣቸው ገልጸዋል፡፡ በኦዲቱ በናሙና ከታዩ ግቢዎች መካከልም በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ደረቅ ቆሻሻ በማስወገድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች አስፈላጊው የመከላከያ ቁሳቁስ ማለትም የእጅ ጓንትና የአፍ መሸፈኛ በተማላ መልኩ ሳያደርጉ ስራቸውን ሲያከናውኑ እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

62. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሲቭል ሰርቪስ ደንብ መሰረት ለጽዳት ለሰራተኞች ከዐይን መነጸር በስተቀር የመከላከያ ቁሳቁሶች ተሟልቶ እንደሚሰጣቸው፤ሆኖም የተሰጣቸውን የመከላከያ ቁሳቁሶች በአግባቡ ያለመጠቀም ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

### *የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በየኳዳናው ዳርና በሌሎች የተማሪዎችና ሠራተኞች ማዘውተሪያ ስፍራዎች የተቀመጡ መሆኑን በተመለከተ*

63. ምልክት የተደረገባቸው የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ግቢዎች መተላለፊያ ቦታዎች እና በሌሎች የተማሪዎችና ሠራተኞች ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሊቀመጡ ይገባል፡፡ ሆኖም በዩኒቨርሲቲው ደረጃቸውን የጠበቁ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ወጥ በሆነ መልኩ አልተቀመጡም፡፡

64. ኦዲቱ ቡድኑ በናሙና በአካል ከታዩት የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አልፎ አልፎ ትናንሽ ካርቶኖች ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ የተቀመጡ ቢሆንም፣ ምልክት የተደረገባቸው የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በኳዳና ዳርና በተማሪዎች ማዘውተሪያ ስፍራ በተገቢው መልኩ አልተቀመጠም (ምስል 1:)፡፡



ምስል 1፡ ለቆሻሻ ማጠራቀሚያ በሚል የተቀመጡ ካርቶኖች (አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት)

65. ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ቦታዎች የሚመነጩ የቆሻሻ አይነቶችን መሰረት በማድረግ ለማጠራቀሚያ/ማከማቻ አስፈላጊ የሆኑ ቆሳቁሶች እንዲሟሉ ባለመደረጉ ቆሻሻዎች እንዲዝረከረኩ ከማድረጉም በላይ በአይነት በመለየት ለመሰብሰብ እና ለማስወገድ እንዳይቻል፤ እንዲሁም ዩኒቨርስቲው ቆሻሻ ለሚያስወግዱ ሰራተኞች የሚሰጣቸውን

66. የመከላከያ ቁሳቁስ እንዲጠቀሙ አስፈላጊውን ግንዛቤ እንዲያገኙ በማድረግ ክትትል እና ቁጥጥር ባለመድረጉ ሠራተኞቹ የሚሰጣቸውን ቁሳቁስ በአግባቡ እንደማይጠቀሙ በማድረግ ሠራተኞቹ ለተለያዩ ጉዳቶች ያጋልጣቸዋል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸውን ቆሻሻዎች ጥቅም ላይ ለማዋል ሁኔታዎችን ያመቻቸ መሆኑን በተመለከተ

67. በተቻለ መጠን በዩኒቨርሲቲው የሚመነጩ ቆሻሻዎችን እንደገና በመጠቀም ለኃይል፣ ለማዳበሪያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ሊውሉ የሚቻልበትን ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

68. ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸው የሽንት ቤት ፍሳሾች፣ የምግብ ትርፍራፊዎች እና ሌሎችም እንደገና መልሶ በመጠቀም ለሃይል፣ ለማዳበሪያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉበት አሠራር ወጥ በሆነ መልኩ ሁሉንም ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን ቆሻሻዎች ባካተተ ሁኔታ አላመቻቸም፡፡

69. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት የጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ት/ቤት፣ የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ፣ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ፣ የንግድ ስራ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት፣ አቃቂ የሀገር ልማት ፕሮጀክትና ደብረ-ዘይት የእንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ ደረቅ ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ለሃይልና ለማዳበሪያና ለሌሎች አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉበት ሁኔታ አለመመቻቸቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

70. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በዩኒቨርስቲው ቆሻሻን እንደገና መልሶ የመጠቀም ጥረት እየተደረገ መሆኑንና ለአገልግሎት የማይፈለጉ ወረቀቶችን መልሰው ስራ ላይ ለሚያውሉ ሶስተኛ ወገኖች የሚተላለፍበት ሁኔታ መኖሩ፤ ነገር ግን አስተላለፉ ወጥነት ባለው መልኩ እየተከናወነ እንዳልሆነ ገልጸዋል፡፡

71. ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸው ቆሻሻ በአይነትና በባህሪ በመለየት መልሶ በመጠቀም ለሃይል፣ ለማደበሪያና ለሌሎች አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉበትን ወጥ የሆነ ስርዐት ባለመዘርጋቱ ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅምና ለአከባቢ ብክለት መቀነስ ላይ አሉታዊ ተጽኖ ይፈጥራል፡፡

## የደረቅ ቆሻሻ ሲጓጓዝ እና ሲከማች እንዲሸፈን እና በወቅቱ እንዲነሳ ማድረጉን በተመለከተ

### *ቆሻሻዎች ሞልተው ሳይዝረከረኩ በየወቅቱ እንዲነሱ ማድረግን በተመለከተ*

72. ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ሳይዝረከረክ ቆሻሻው በየወቅቱ መነሳቱ ሊረጋገጥ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ቆሻሻዎች የሚይዙ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ሲንቀሳቀሱ እንዲሸፈኑ ሊያደረግ ይገባል፡፡

73. በዩኒቨርሲቲው ስር በሚገኙ እና በኦዲቱ በናሙና ከታዩ በጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ዋና ግቢ፣ ንግድ ስራ ኮሌጅ የሚመለከታቸው የስራ አካላት ቆሻሻ በየጊዜው እንደሚነሳ የገለጹ ቢሆንም፣ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ቆሻሻ የሚዝረከረክና በወቅቱ የማይነሳ ሲሆን፣ አቃቂ የሀገር ልማት ፕሮጀክት ፣ደብረ ዘይት

እንስሳት ህክምነና ግብርና ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት እና የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ ቆሻሻ በብዛት ሜዳ ላይ ተጥሎ ተዝረክርኮ ይታያል (ምስል 2 እና 3) ፡፡ እንዲሁም ቆሻሻን የሚይዙ ማጠራቀሚያዎች ሲጎዝዙ ቆሻሻ እንዳይዝረከረክ፣ አከባቢን እንዳያበላሹና እንዳይበክሉ እንደሸፈኑ አልተደረገም፡፡




ምስል 2፤ ቆሻሻ በአግባቡ ሳይሰበሰብ በገንዳ አጠገብ ተዝረክርኮ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ




ምስል 3፡ ቆሻሻ በአግባቡ ሳይሰበሰብ በየቦታው ተዝረክርኮ /ደብረ ዘይት የእንስሳት ህክምና እና ግብርና ኮሌጅ/

74. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በዘህ ረገድ በዩኒቨርስቲው መሻሻል የሚደረግ ጥረት እንዳለ፤ ነገር ግን አቅም ያነሳቸውም የጽዳት ሠራተኞች ገንዳው ላይ መድፋት ባለመቻላቸው መሬት ላይ ጥለው የሚሄዱበት ሁኔታ እንደሚታይ፤ ቆሻሻው የሚወገደው በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት በመሆኑ ማህበራቱ አልፎ አልፎ በወቅቱ ስለማይመጡ እና እነሱን የሚከታተልና እርምጃ የሚወስድ አካል ባለመኖሩ ገንዳው ሞልቶ የሚዝረከረክበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

75. ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ሞልተው ሳይዝረከረኩ በየጊዜው እንዲነሱ ክትትል አለመደረጉ እንዲሁም የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ሲንቀሳቀሱ አለመሸፈናቸው ቆሻሻ እንዲዝረከረክ፣ አከባቢ እንዲበክልና እንዲበላሽ በማድረግ ለስራና ለትምህርት ምቹ ሁኔታ እንዳይኖር እያደረገ ይገኛል፡፡

## የፍሳሽ ቆሻሻዎች አወጋገድ በተመለከ፤

### *በቂና ተስማሚ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ሁኔታ እና ቦታዎች የተመቻቹ እና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉን በተመለከተ*

76. በዩኒቨርሲቲው በቂና ተስማሚ የመጸዳጃ ቤት፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መገልገያዎች በቦታው ሊያዘጋጅ እና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆናቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

77. ሆኖም በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የመጸዳጃ ቤቶች በተወሰነ መልኩ ተስማሚና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት በበቂ ሁኔታ እየሰጡ አይገኙም (ምስል 4 እና 5 )፡፡




**ምስል 4 እና 5፡ በተገቢው ሁኔታ ያልጸዳ እና በፍሰሽ ቆሻሻ የተበከለ መጸዳጃ ቤት(ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ)**

78. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ መጸዳጃ ቤቶች በቆሻሻ የተሞሉና ለአጠቃቀም አስቸጋሪ መሆናቸውን እንዲሁም የመታጠቢያ ቤቶች ቱቦ፣ ብረቶችና በሮች የዛጉና እየተፈረካከሱ በመርገፍ ላይ እንደሚገኙ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

79. ስለ ሁኔታው የዩኒቨርስቲው የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በዩኒቨርሲቲው በቂና ተስማሚ የመጸዳጃ ቤት እንዲኖር ብዙ ጥረት መደረጉን፤ ከተማሪዎች መኖሪያ ህንጻ በተጨማሪ ውጭ የመጸዳጃ ቤቶችን በመገንባት ችግሩን ለማቃለል መሞከሩን፤ ነገር ግን በቂ ናቸው ማለት እንደማይቻል፤ ተስማሚ ለማድረግ የተወሰዱ እርምጃዎች መኖራቸውን እና ከዚህም ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች በሚያመች ሁኔታ መሠራቱን፤ በአንጻሩ ደግሞ ህንጻዎቹ ከማርጀታቸው የተነሳ አገልግሎት የማይሰጡ መጸዳጃዎች እንዳሉ፤ እንዲሁም በቂ ዝግጅት ሳይኖር ማለትም የዩኒቨርሲቲው የቅበላ አቅም ሳይገናዘብ የተማሪዎች ቁጥር ከዓመት ዓመት የሚጨምርበት ሁኔታ በመኖሩ ያለመመጣጠን በስፋት የሚታይ መሆኑ እንዲሁም የተማሪዎችም የአጠቃቀም ችግር አስተዋጽኦ በማድረጉ ችግሩን ለማቃለል እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

80. በዩኒቨርሲቲው የተገነቡት የመፀዳጃ ቤቶች ቀጣይነትባለው ሁኔታ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ የሚደረገው ክትትል ደካማ በመሆኑ በተሟላ መልኩ አገልገሎት እየሰጡ ባለመሆናቸው የየኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ ይህን መሠረታዊ ግልጋሎት በቅርብ እና በተሻለ ሁኔታ እንዳያገኝ እያደረጉት ይገኛሉ፡፡

## *የፍሳሽ  ቆሻሻዎችን መሬት ላይ እንዳይፈሱ ማድረጉን በተመለከተ*

81. ከተለያዩ የዩኒቨርስቲው የስራ ክፍሎች የሚመነጩ ፍሳሽ ቆሻሻዎች ከተዘረጋላቸው የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች በመውጣት ከመሬት በላይ እንዳይፈሱ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ ሆኖም ከተለያዩ የዩኒቨርስቲው የስራ ክፍሎች የሚመነጩ ፈሳሽ ቆሻሻዎች ከተዘረጋላቸው የፍሳሻ ማስወጋጃ ቱቦዎች በመውጣት መሬት ላይ እንዳይፈሱ ወጥ በሆነ መልኩ ጥንቃቄ አላደረገም፡፡

82. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት መካከል ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከተማሪዎች እና ከዶክተሮች መኖሪያ የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ የወንዶች እና ሴቶች  የጋራ ሽንት ቤት የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች ከተዘረጋላቸው የፍሳሽ ቱቦዎች በመውጣት መሬት የሚፈሱ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ግቢ በአንድ ህንጻ ላይ የሚገኙ ሽንት ቤቶች ፍሳሽ ከተዘረጋላቸው ማስወገጃ ቱቦዎች በመውጣት በህንጻው ግርግዳና መሬት  ላይ የሚፈሱ መሆኑን በአካል ቦታው ድረስ በመሄድ ለመመልከት ተችሏል (ምስል 6 እና 7)፡፡






**ምስል 6 የሽንት ቤት ፍሳሽ ግርግዳ ሲያበላሽ (ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ)ምስል7 ፍሳሽ ቆሻሻዎች ከዋናው መስመር ጋር ሳይገናኙ ሜዳ ላይ ይፈሳሉ(የኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት)**

83. በኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ  ልማት ኢንስቲትዩት  የፍሳሽ ቆሻሻ ቱቦ ከከተማው የቆሻሻ ማስወገጃ ጋር በትክክል ያልተገናኘ በመሆኑ ፈሳሽ ቆሻሻው ግቢው ውስጥና ውጭ ላይ መሬት ላይ ፈሶ ታይቷል፡፡

84. ስለ ጉዳዩ የዩኒቨርስቲው የሚመለከታቸው  የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ችግሩ አልፎ አልፎ የሚከሰት መሆኑን፤  የሚከሰትበት ምክንያትም የመተላለፊያ ቱቦን የሚዘጉ የተለያዩ ነገሮች ሲገቡ የተዘጋበትን ቦታ ለማግኘት ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ እና ተገቢው ጥገና እስከሚደረግ ድረስ  ቆሻሻው መሬት ላይ ፈሶ እንደሚታይ ገልጸዋል፡፡

85. ስለሆነም ፈሳሽ ቆሻሻዎች ከተዘረጋላቸው መስመር እንዳይወጡ አስፈላጊው ጥንቃቄ አለመደረጉ ፍሳሽ ቆሻሻዎች መስመራቸው ለቀው በመፍሰስ አካባቢን ከመበከላቸው በተጨማሪ  የፍሳሽ መስመሩ የሚያልፍባቸውን የህንፃ ክፍሎች የመጉዳትና  መጥፎ ሽታ በመፍጠር በዩንቨርሲቲውን ማህበረሰብ ጤና ላይ  ጉዳት እንዲያስከትሉ ያደርጋል፡፡

## ከዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ስራ ክፍሎች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች ጉዳት እንዳያስከትሉ ጥረት የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ

### *የአደገኛ ቆሻሻን ከምንጩ ለመቀነስ የሚያደርገውን ጥረት በተመለከተ*

86. የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓት ዋናው መርህ  ቆሻሻን ከሚመነጭበት ቦታ ብዛቱን እና አደገኝነቱን መቀነስ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻው ከሚመነጭበት ቦታ የሚቀንስበት መንገድ ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ሆኖም አደገኛ ቆሻሻ ከሚመነጭበት ብዛቱንና አደገኛነቱን ለመቀነስ ተገቢው ጥረት አልተደረገም፡፡

87. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ እና የንግድ ስራ ት/ቤት የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶች በብዛት በክሊኒክ ውስጥ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡ በአዲስ አበባ  ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከምርመር ቤተ ሙከራዎች የሚወጡ ምርምር የተደረገባቸው ኬሚካሎች በመጋዘንና  በቤተሙከራዎች ውስጥ ተከማችተው ይገኛሉ(ምስል 8፣9)፡፡



ምስል 8፡ምርምር የተደረገባቸው የተለያዩ ኬሚካሎች ለረጅም ጊዜ ሳይወገዱ በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ(አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት)



ምስል 9፡ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶች  ሳይወገዱ ለረዥም ጌዜ በክሊኒክ ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ (አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዋና ግቢ)

88. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣  መድሃኒቶች የአገልግሎት ጊዜያቸው ሲቃረብ ለሆስፒታሎች አከፋፍሎ በወቅቱ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ የማድረግ እንዲሁም በእርዳታ የሚመጡ የተለያዩ ዕቃዎችና ኬሚካሎች ሲገቡ አስፈላጊነታቸውና ጠቃሚነቻው ታውቆ እንዲገቡ የማድረጉ ሁኔታ

ላይ ክፍተት መኖሩን፤ ለዚሁም ወጥ የሆነ የቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብ፣ አጓጓዝና አወጋገድ የአሠራር ሥርዓት በዩኒቨርሲቲው ያልተዘረጋ በመሆኑ ቆሻሻ ከሚመነጭበት ቦታ አደገኛነቱን ለመቀነስ እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

### *ከማስተማሪያ የምርምር ቤተ-ሙከራዎችና ከክሊኒክ የሚወጡ አደገኛ የፍሳሽ ቆሻሻዎች ጉዳት እንዳያስከትሉ ጥረት የሚደረግ መሆኑን በተመለከተ*

89. ዩኒቨርሲቲው ከማስተማሪያ የምርምር ቤተ-ሙከራዎችና ከክሊኒክ የሚወጡ አደገኛ ፍሳሽ እና ሌሎች ቆሻሻዎች ከመወገዳቸው በፊት በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

90. በኦዲቱ እንደታየው፤ ከዩኒቨርሲቲው ማስተማሪያ ምርምር ቤተ ሙከራዎች እና ክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ ከመግባታቸው በፊት የያዙት ጎጂ ንጥረ ነገር በሰውና በአከባቢ ላይ ጉዳት አንዳያስከትሉ አስፈላጊው ጥንቃቄ አልተደረገም፡፡

91. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የተፈጥሮ ሳይንስና ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከምርምር ቤተ ሙከራዎች እና ክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች ጉዳት የማያስከትሉ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ወደ ፍሳሽ ቱቦዎች ይለቀቃሉ (ምስል 10)፡፡

ምስል 10 ከላበራቶሪ እና ከቤተሙከራ የሚወጡ ፈሳሽ አደገኛ ቆሻሻዎች (ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ)



92. ስለ ሁኔታው የሚመለከታቸው የዩኒቨርስቲው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ፈሳሽ ቆሻሻዎችን ለማከም የአቅም ማነስ መኖሩ ማለትም የባለሙያ አለመኖር፣ በእቅድ አለመያዙ እና አስፈላጊው በጀት አለመመደብ እንዲሁም የአሰራር ስርአት አለመዘርጋት ዋነኛ ምክንያቶች እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡

### *ከዩኒቨርሲቲው ጤና ተቋማት የሚመነጩ ስለታም የሆኑ አደገኛ ቆሻሻዎች አወጋገድን በተመለከተ*

93. ከዩኒቨርስቲው የጤና ተቋማት የሚመነጩ ሌሎች አደገኛ እና ሥለታማ ቆሻሻዎች የማሰባሰብ ተግባር በየቀኑ ሊከናወንና በማጓጓዝ እና በማስወገድ ተግባራት ወቅትም ጉዳት እንዳያስከትሉም ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡

94. ከዩኒቨርሲቲው ጤና ተቋማት የሚመነጩ ሌሎች አደገኛ እና ስለታም ቆሻሻዎች ተለይተው የሚሰበሰቡና የሚከማቹ ቢሆንም፣ በየቀኑ ጉዳት እንዳያስከትሉ ጥንቃቄ

በማድረግ የማጓጓዝና የማስወገድ ተግባር የማይከናወንና ከሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች ጋር አብሮ የሚወገድ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

95. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አደገኛ ቆሻሻ ሳይወገድ በክሊኒኩ ውስጥ በብዛት ተከማችቶ መታየቱ፤ እንዲሁም በንግድ ስራ ኮሌጅ እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶች ተሰብስበው ለረጅም ጊዜ ሳይወገዱ በክሊኒክ ውስጥ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡ ይህም ለማስወገድ ተግባር ተገቢው ትኩረት አለመሰጠቱን፤ እንዲሁም የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ፣ አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ አርቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንሲቲትዩት እና ደብረ ዘይት እንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ ስለታም ቆሻሻዎች በባለሙያ ተለይተው የሚሰበስቡና የሚከማቹ ቢሆንም፣ የሚወገዱት ከሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች ጋር አብሮ በማቃጠል እንደሆነ ለመመልከት ተችሏል፡፡

96. በኦዲቱ በናሙና የተመረጡት የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በዩኒቨርሲቲው አደገኛና ስለታም ቆሻሻዎች ለይቶ ማስወገድን በተመለከተ ቀደም ሲል ሙከራዎች እንደነበሩ፤ አሁን ግን ሁሉም ቆሻሻዎች በአንድ ላይ የሚወግዱ መሆናቸውን የተገለጸ ሲሆን፣ በተጨማሪም የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የበላይ የሥራ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ አደገኛ ቆሻሻን ለይቶ ማስወገድ የግንዛቤ አለመኖር እና የባለሙያ አለመመደብ አንዱ ምክንያት ሲሆን፤ ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋቱም ዋናው የችግሩ መንስኤ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

## ***ከክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የተለየ ሥፍራ የተዘጋጀ መሆኑን በተመለከተ***

97. ዩኒቨርሲቲው ከክሊኒኮች ለሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የተለየ ሥፍራ ሊያዘጋጅ ይገባል፡ ሆኖም ዩኒቨርሲቲው ከተማሪ ክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች ከባህሪያቸው አንጻር በአከባቢና በዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ የሚወገዱበት የተለየ



ምስል ፲፡ ሊወገዱ የሚገቡ የተለያዩ ሹል እና ስለታም የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች በካርቶን በመጸዳጃቤቶች ተከማችተው ለረጅም ጊዜ የተቀመጡ (አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት)

ስፍራ አላዘጋጀም፡፡

98. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት የአዲስ አበባ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ፣ የአዲስ አበባ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት፣ደብረ ዘይት እንስሳትና ግብርና ኮሌጅ እንዲሁም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ዋና ግቢ ክሊኒክ የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የተለየ ስፍራ የላቸውም (ምስል 11)፡፡

99. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የተጎበኙ የተለያዩ ኮሌጆች የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በዩኒቨርሲቲው አደገኛና ስለታም ቆሻሻዎች ለይቶ የማስወገድ ተግባር በፊት ጊዜ ሙከራዎች እንደነበሩ፤ አሁን ግን ሁሉም ቆሻሻዎች በአንድ ላይ የሚወገዱ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

100. በተጨማሪም ሁኔታውን በተመለከተ የዩኒቨርሲቲው የበላይ ሃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ አደገኛ ቆሻሻን ለይቶ ለማስወገድ በዩኒቨርሲቲው ወጥ የሆነ የአሠራር ሥርዓት አለመዘርጋት እና የግንዛቤ አለመኖር አስተዋጽኦ ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

101. ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው አደገኛ ቆሻሻዎች ከምንጫቸው እንዲቀንሱ ጥረት አለመደረጉ፤ የማስተማሪያና የምርምር ቤተ ሙከራዎች እና ኪሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ፍሳሽ ቆሻሻዎች ጥንቃቄ ተደርጎ ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ እንዲገቡ ባለመደረጉ እንዲሁም ከጤና ተቋማት የሚመነጩ አደገኛ ቆሻሻዎች የማሰባሰብና የማስወገድ ተግባር በወቅቱ አለመከናወኑ በዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ በተለይም ክምችቱ በሚገኝበት አካባቢ በሚገኙት ላይ የከፋ የጤና ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡

## ከምግብ ቤቶች የሚመነጩትን ከምግብ ጋር የተያያዙ ቆሻሻዎች አወጋገድ በተመለከተ

102. ዩኒቨርሲቲው ከምግብ ቤቶች የሚመነጩ ከምግብ ጋር የተያያዙ ደረቅ ቆሻሻ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ ማለትም የሚሰበሰበውን ቆሻሻ በቀላሉ ለመለየት በሚያስችል መልኩ ሊሰበስብ፣ ሊያጓጉዝና ሊያስወገድ ይገባል፡፡

103. ከምግብ ቤት የሚመነጩ ከምግብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ደረቅ ቆሻሻዎች ለብቻ ተለይተው የሚሰበሰቡ የሚጓጓዙ ቢሆኑም የሚከማቹትና የሚወገዱት ግን ለብቻ አከባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መልኩ ሆነው አልተገኙም፡፡

104. በኦዲቱ በናሙና በአካል ከታዩት የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ፣በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ እና ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተረፈ ምግብ ከደረቅ ቆሻሻዎች ተለይተው እንዲከማቹና እንዲወገዱ አልተደረገም፡፡ በአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ ፣በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ፣ በጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ፣በአቃቂ ሀገር ልማት ፕሮጀክተ ፣ደብረ ዘይት እንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩትና የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ በምግብ ዝግጅት ወቅት የሚመነጩ ቆሻሻዎች ከሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች ተለይተው እንዲከማቹ በማድረግ እንዲወገዱ አልተደረገም (ምስል 12 እና 13)፡፡






ምስል 12 እና 13፤ ከምግብ ቤት የሚወጡ ቅድመ እና ደህረ ምግብ ቆሻሻዎች ከደረቅ ቆሻሻ ጋር የሚጣሉና የተዝረከረኩ( ኢ.አ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ እና ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ)

105. ስለ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በዩኒቨርስቲው የቆሻሻ አወጋገድ የአሰራር ስርዐት አለመዘርጋት እንዲሁም በተያያዥ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የአሰራር ደንብ አለመኖር እና እራሱን የቻለ የቆሻሻ መድፊያ እና ማንሻ ጊዜ የሚገልጽ መመሪያ ባለመዘጋጀቱ እንደሆነ በማለት ገልጸዋል፡፡

106. ስለሆነም ለተለያዩ ጠቀሜታዎች ሊውሉ የሚችሉ ከምግብ ቤት የሚወጡ ደረቅ ቆሻሻዎች አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መልኩ ተለይተው እንዲሰበሰቡና እንዲከማቹ በማድረግ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

## የደረቅ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች የተገነቡ እና አስፈላጊውን ጥገና የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ

107. የፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ደረጃን መሠረት በማድረግ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ሊገነቡ እና አስፈላጊው ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡ ሆኖም በናሙና

በታዩት የዩኒቨርስቲው ግቢዎች ለደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ የተገነቡ ማቃጠያዎች አስፈላጊው ክትትል እና ጥገና በወቅቱ ባለመደረጉ በጉዳት ላይ መሆናቸውና የተወሰኑትም ደግሞ ማቃጠያ የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

108. በኦዲቱ በናሙና ከታዩት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ፣ የደብረ ዘይት እንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ እና የኢተዮጵያ አርክቴክቸርና ከተማ ልማት አንስቲትዩት የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ ያላቸው ቢሆንም፣ ደረጃ ጠብቀው የተገነቡ አይደሉም፡፡ የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ እና አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንሲትትዩት የቆሻሻ ማቃጠያ ያልገነቡና ቆሻሻ ሜዳ ላይ የሚያቃጥሉ መሆኑን በግቢዎቹ በተደረገ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል (ምስል14 ) ፡፡



ምስል 14፤ ሁሉም አይነት ቆሻሻ ሜዳ ላይ የሚቃጠል ስለመሆኑ (አዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት)

109. ደብረ ዘይት እንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ የቆሻሻ ማቃጠያው በር ተገንጥሎ የተጣለና የተሰባበረ፤ የኢትዮጵያ አርቴክቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት ማቃጠያው ግንድ የወደቀበትና የተሰባበረ ስለመሆኑ፤ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩሊቲ የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ የተሰባበረና አስፈላጊው ክትትልና ጥገና እንዳልተደረገላቸው የኦዲት ቡድኑ በአካል ቦታው ድረስ በመሄድ ለመመልከት ተችሏል (ምስል 15 እና 16)፡፡




ምስል 15 እና 16፡ የተሰባበሩ እና ጥገና ያልተደረገላቸው የቆሻሻ ማቃጠያ ቦታዎች (ደብረ ዘይት እንስሳት ህክምናና ግብርና ኮሌጅ እና የኢትዮጵያ አርክቴክቸር እና ከተማ ልማት ኢንሲቲትዩት)

110. በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው የታዩ ግቢዎች የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፣ ከጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በስተቀር የአካባቢ ጥበቃን ደረጃ ጠብቆ የተገነባ የቆሻሻ ማቃጠያ የሌላቸው መሆኑን፤ ነገር ግን በሌሎቹ ተቋማት ማቃጠያዎች ያሉ ቢሆኑም ተማሪው አነስተኛ በነበረበት ዘመን የተገነቡ እና የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ መጠን ዕድገትን ባገናዘበ ሁኔታ እንዲሻሻሉ ያልተደረገ መሆኑ፤ እንዲሁም በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ የቦታ ጥበት በመኖሩ የቆሻሻ ማቃጠያ መስራት እንዳልተቻለ ገልጸዋል፡፡

111. ስለ ሁኔታው የዩኒቨርሲቲው የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ለመገንባት ብዙ የመጸዳፍ ልውውጥ መደረጉን፤ ሆኖም የአፈጻጸም ክፍተት በመኖሩ እና ሥርዓት አለመዘርጋቱም ዋነኛው ችግር እንደሆነ፤ እንዲሁም የቆሻሻ ማቃጠያ አስገንብቶ በባለቤትነት ክትትል የሚያደርግ እራሱን የቻለ ተጠያቂነት ያለው የስራ ክፍል ተለይቶ በግልጽ ስለማይታወቅና እንደ ተደራቢ ስራ ስለሚታይ ለተገነቡት ማቃጠያ ቦታዎች በቂ ክትትል ያልተደረገላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

112. ስለሆነም በዩኒቨርሲቲው የፌዴራል የአካባቢ ጥበቃ ደረጃን መሠረት በማድረግ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲገነቡ ባለመደረጉ እንዲሁም ላሉት ማቃጠያዎች አስፈላጊ ክትትልና ጥገና ስለማይከናወንላቸው ቆሻሻ በሜዳ ላይ እንዲቃጠልና አከባቢያዊ ተጽኖ እንዲያስከትል እያደረገው ይገኛል፡፡

## ከዩኒቨርሲቲው ደረቅ ቆሻሻን በማስወገድ ተግባር ላይ የተሰማራው አካል ህጋዊ ፈቃድ ያለው መሆኑን በተመለከተ

113. ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ፣ ጥቅም ላይ በማዋል ወይም በማስወገድ ተግባር ላይ የሚሰራ ማንኛውም ድርጅት/ሰው ከሚመለከተው አስተዳደር አካል በቅድሚያ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡

114. በዩኒቨርሲቲው ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝና በማስወገድ ተግባር ላይ የተሰማራው ድርጅት/ሰው ከሚመለከተው አስተዳደር አካል ፈቃድ ያለው መሆኑን ዩኒቨርስቲው ተጠይቆ መረጃ አላቀረበም፡፡

115. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በዩኒቨርስቲው ቆሻሻን አጓጉዘው የሚያስወግዱት ከቀበሌ ተደራጅተው

የሚመጡ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት መሆናቸውን እና ከቀበሌ የሚጻፍላቸውን ደብዳቤ መሠረት በማድረግ ውል በመግባት ሥራውን እንዲያከናውኑ እንደሚደረግ የገለጹ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻውን ከሚያስወግዱ አካላት ጋር የገባው ውል የቀረበ ቢሆንም ከቀበሌ የተፃፈላቸው መረጃ ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም ዩኒቨርሲቲው ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝና በማስወገድ ተግባር ላይ የተሰማራው ድርጅት/ሰው ከሚመለከተው አስተዳደር አካል ፈቃድ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

116. ከዩኒቨርሲቲው ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ፣ ጥቅም ላይ በማዋል ወዘተ የማስወገድ ተግባር የሚያከናውነው አካል ከሚመለከተው አስተዳደር አካል በቅድሚያ ፈቃድ ያለው መሆኑ የማይረጋገጥ ከሆነ የቆሻሻ ማስወገዱ ተግባር በተገቢው ሁኔታ እንዳይከናወን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## በዩኒቨርሲቲው የሚከረፋ ሽታ እንዳይኖር ማድረግን በተመለከተ

117. የሚከረፋ ሽታ ምንጮች ላይ ቁጥጥር ሊያካሄድ ይገባል፡፡ ሆኖም የሚከረፋ ሽታ ምንጭ በአከባቢና በዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ላይ የሚያስከትለውን ጠንቅ ለመግታት በዩንቨርሲቲው ክትትልና ቁጥጥር ተደርጎበት አልተገኘም፡፡

118. በኦዲቱ በናሙና ከታዩት ጥቁር አንበሳ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከተማሪዎች መኖሪያ፣ከሆስፒታሉ ላበራቶሪ፣ ከቤተ ሙከራዎች፣ ከምግብ ቤቶችና ከሽንት ቤት የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች በአንድ ላይ ተከማችተው በአከባቢ ላይ መጥፎ ሽታን የፈጠሩ መሆናቸውን፤ እንዲሁም ከሆስፒታሉ የሚወጡ አደገኛ ኢንፌክሽን ሊያስከትሉ የሚችሉ ቆሻሻዎችና ተረፈ ምግቦች በገንዳ ላይ የሚጣሉ ሲሆኑ፣ በተማሪዎች መኖሪያ አከባቢ ላይ የሚከረፋ ሽታ የፈጠሩ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

119. በተጨማሪም የኢትዮጵያ አርክቴቸርና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት ግቢው ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ቱቦ ከከተማው ዋና መስመር ጋር ያልተገናኘ በመሆኑ ፍሳሽ ቆሻሻው ግቢ ውስጥ እየፈሰሰ በአከባቢው ላይ መጥፎ ሽታን የፈጠረ መሆኑ፣ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ተረፈ ምግብ ተከማችቶ ተጥሎ በአከባቢው ላይ መጥፎ ሽታ የፈጠረ መሆኑ ለመመልከት ተችሏል፡፡

120. በመሆኑም መጥፎ ጠረን መከሰቱ በዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ላይ የሚያስከትለውን ጠንቅ ለመግታት አስፈላጊው ክትትል ባለመደረጉ በማህበረሰቡ ጤና ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡

# ክፍል ሦስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

121. የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቆሻሻ አወጋገድ በእስትራቴጂክ እቅድ ተይዞ ወጥ በሆነ ሁኔታ እየተሰራ ባይሆንም፣ አንዳንድ የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸው የሚበረታታና የሚደገፍ ነው። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ የአፈጻጸም ውጤታማነት በኦዲቱ በሚገመገምበት ወቅት ከዚህ በታች የሚመለከቱት ዋና ዋና የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል።

- ዩኒቨርሲቲውን የቆሻሻ አያያዝ አጓጓዝና አወጋገድ በተመለከተ የአሰራር ስርአትና መመሪያ ያልዘረጋ እና ተግባራዊ ያልተደረገ በመሆኑ ቆሻሻን በአይነትና በባህሪ ለይቶ የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣ የማጓጓዝ ፣የማስወገድና መልሶ የመጠቀም ስራ በተፈለገው መጠን እንዳይከናወን ማድረጉ፤
- ዩኒቨርሲቲው የአካባቢ ዘላቂነት በቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ በስትራቴጂክ ዕቅድ አካቶ ያላቀደና እንዲሁም የአካባቢ ዘላቂነትን ለማስረጽ የሜይንስትሪሚንግ (mainstreaming) ስራ በቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ተግባራዊ ያላደረገና በስራው ላይ የሚታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶችን ያላካተተ በመሆኑ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰርጽና የአካባቢ ዘላቂነት አላማ በዩኒቨርስቲው ለማሳካት አለማስቻሉ ፤
- በዩኒቨርሲቲው በአካባቢ ዘላቂነት ለተቋቋሙ ክበባት ሙያዊ ድጋፍ የማድረግ፣ በጋራ ተቀናጅቶ የመስራትና የማሳተፍ ስራ በበቂ ሁኔታ ያልተስራ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝና በማስወገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች፣ ለተማሪዎች፣ ለባለ ድርሻ አካለት ቆሻሻ በአይነትና በባህሪ ደረቅ፣ ፈሳሽና አደገኛ የሆኑትን በመለየት እንዴት መሰብሰብ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝና ማስወገድ እንዳለባቸው ለማወቅ የሚችሉበት በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ስልጠና ያልሰጣቸው መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ሰንሰለት ስራዎች የሚመለከቱ ተግባራት በግልጽ ኃላፊነትን በግልጽ አለማስቀመጡ ደረቅ ቆሻሻ በማስወገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኖች አስፈላጊውን የመከላከያ ቁሳቁሶች እንዲሁም የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቆሳቁሶችችን በተሟላ መልኩ የሌሉ መሆኑን፣ በተጨማሪም ቆሻሻ በሚጓጓዝበት ወቅት የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች እንዲሸፈኑ የማይደረግ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው የሚያመነጫቸው ቆሻሻዎች በተቻለ መጠን እንደገና መልሶ በመጠቀም ለኃይል፣ ለማዳበሪያና ለሌሎች አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ወጥ በሆነ መልኩ ያላመቻቸ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የመጸዳጃ ቤቶች ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተስማሚና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያደርገው ክትትል የላላ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው አደገኛ ቆሻሻ ከሚመነጭበት ቦታ ብዛቱንና አደገኛነቱን ለመቀነስ የሚቻልበት መንገድ ያልዘረጋ መሆኑ፣

- ❖ ዩኒቨርሲቲው ለደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ የፌደራል አካባቢ ያወጣውን ደረጃ ተከትሎ ያልገነባና አገልግሎት እንዲሰጥ ያላደረገና እንዲሁም ማቃጠያዎቹ ጥገና በሚያስፈልጋቸው ወቅት አስፈለጊው ክትትልና ጥገና የማይደረግላቸው መሆኑ፣
- ❖ ዩኒቨርሲተው ከተማሪዎች መኖሪያ ፣ከክሊኒክ ላብራቶሪ፣ ከምርምር ቤተ ሙከራዎች ፣ ከምግብ ቤትና ከሽንት ቤቶች የሚወጡ የሚከረፉ ሽታ የሚፈጥሩት ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ምንጮች ላይ በዩኒቨርስቲው የሚደረገው አስፈላጊው ቁጥጥርና ክትትል የላላ መሆኑ፣

የዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል በኦዲቱ ወቅት የታዩትን የአሰራር ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

- በዩኒቨርሲቲው የሚመነጨውን ቆሻሻን ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል፣ጉዳት እንዳያመጣ ለማምከንና ለማስወገድ የሚያስችለውን የአሰራር ስርዐት በጥናት ሊዘረጋና ይህንን ተግባር ወጥ በሆነ መንገድ ሊከናወን የሚችልበት መመሪያ በማውጣት ተግባራዊነቱን ተከታታይ ክትትል በማድረግ ጭምር ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

- የአከባቢ ቀጣይነት (environmental sustainability) እንዲኖር ሁሉንም የዩኒቨርስቲውን ማህበረሰብ አካቶ ሁሉን አቀፍ የሆነ የአከባቢ ቀጣይነት ስትራቴጂክ እቅድ ሊያቅድ፤ የአከባቢ ቀጣይነትን በቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ክንውን ሂደት ውስጥ በሁሉም ዘንድ የባለቤትነት ስሜት ለማስረጽ የሜንስትሪሚንግ ስራ በዕቅድ ተግባራዊ ሊያደርግ፤ በዕቅድ ክንውን ሪፖርቱ ውስጥ ለሚታዩ የአፈፃፀም ክፍተቶች የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድና በተማሪዎች በሚመሩ የአከባቢ ዘላቂነት ክበበባት ጋር ቀጣይነት ያላቸው ስራዎች በትብብር ተቀናጅቶ የመስራትና የማሳተፍ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡

- የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ መነሻ በማድረግ ምን ያህል ቆሻሻ እንደሚያመነጭና በምን አይነት መንገድ መሰብሰብ፣ መያዝ፣ ማጓጓዝና ማስወገድ እንዳለበት የሚያስችለውን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አቅድ ሊያዘጋጅና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን በመከታተል በዕቅዱ አፈጻጸም ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

- ለተማሪዎች ለሰራተኞች ለባለድርሻ አካላት ቆሻሻን በአይነትና በባህሪ በመለየት እንዴት መሰብሰብ መያዝ ማጓጓዝና ማስወገድ እንዳለባቸውና እንዲሁም አግባብነት ያላቸውን ቆሻሻዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ እንደሚችሉ ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና በሀገር አቀፍ የወጡ ቆሻሻን የሚመለከቱ አዋጆች[2] እና በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የወጡ የቆሻሻ አወጋገድን የሚመለከቱ መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲያከናውኑ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ሊሰራና እንዲሁም ቆሻሻ በመሰብሰብ፣በማጓጓዝና በማሰወገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች ወቅታዊና ተከታታይነት ያለው ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

- በቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ሰንሰለት ስራዎች ለተሠማሩ ሰራተኞች ስራቸውን በአግባቡ ለማከናወንና ተጠያቂነት እንዲኖር የስራ ድርሻ እና ሃላፊነት በግልጽ ለይቶ

---

[2] አዋጅ ቁጥር 513/1999 የደ ረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 300/1995 የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 295/1995 የአካባቢ ጥበቃ አካላትን ማቋቋሚያ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 200/1992 የሕዝብ ጤና አጠባበቅ አዋጅ፣

በማስቀመጥ ተጠያቂነታቸውን አውቀው ስራቸውን እንዲያከናውኑ የስራ ድርሻቸው በጽሁፍ እንዲደርሳቸው ሊያደርግ፤ እንዲሁም ስራቸውን በብቃት ለማከናወን እንዲያስችላቸው ለእጃቸው፣ለአፋቸው እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የመከላከያ ቁሳቁስ ሊያሟላላቸውና እንዲሁም በዩኒቨርስቲው ከተለያዩ ቦታዎች የሚመነጩ የቆሻሻ አይነቶችን መሰረት በማድረግ ቆሻሻ በግቢ ውስጥ እንዳይዝረከረክ፣ መጥፎ ሽታ እንዳይፈጥርና አከባቢን እንዳያበላሽ ለማጓጓዝ ለማጠራቀሚያና ለማስወገጃ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ሊሟሉና ክዳን ባላቸው ማጠራቀሚያዎች እንዲጓጓዙ ሊደረግ ይገባል፡፡

- ❖ ከቢሮ፣ ከተማሪዎች መኖሪያዎች እና ከምግብ ቤት የሚመነጩ ደረቅ ቆሻሻዎችን በአይነት፣ በባህሪና በመለየት በሚችለው አቅም አግባብነት ያላቸውን ቆሻሻዎች እደገና መልሶ በመጠቀም ለኃይል ለማዳበሪያና ለሌሎች አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ❖ በዩኒቨርስቲው የሚገኙ የመጸዳጃ ቤቶች ለዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ተስማሚ በሆነ መልኩ ንጽናቸው የሚጠበቅና አስፈላጊው ክትትል የሚደረግላቸው እና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ አስፈላጊው ጥገና በወቅቱ የሚደረግላቸው ስለመሆኑ ክትትል ሊያደርግና ተገቢውን አገልግሎት የሚሰጡ መሆናቸውን ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- ❖ አደገኛ ቆሻሻዎች ከሚመነጩበት ብዛታቸውና አደገኛነታቸውን ለመቀነስ ወደ አደገኛ ቆሻሻነት ከመቀየራቸው በፊት ከሚመነጩበት ማለትም መድሀኒቶችም ሆኑ ሌሎች ለምርምር ተግባር የሚገዙም ሆነ በዕርዳታ የሚገኙ ኬሚካሎች ሀገር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት አስፈላጊነታቸውና ጠቀሜታቸው ታውቆ በሚያስፈልገው መጠን ማስገባትና የአገልግሎት ጊዜያቸው ማብቂያ ሳይቃረብ ለሌሎች በመስጠት ይህን ማድረግ ካልተቻለ የአገልግሎት ጊዜአቸው እንዳለፈ እንዲወገዱ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ ከዩኒቨርሲቲው የጤና ተቋማት ክሊኒኮች የሚመነጩ አደገኛ ስለታም ቆሻሻዎች በአካቢና በጤና ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ለብቻ በመለየት በየቀኑ እንዲሰበሰቡ፣ እንዲጓጓዙ ሊደረግ እና የሚወገዱበት ስፍራም ሰው በማይበዛበትና ራቅ ያለ ስፍራ በጥንቃቄ ሊሆን ይገባል፡፡
- ❖ ቆሻሻ ሜዳ ላይ እንዳይጣልና እንዳይዝረከረክ ምልክት የተደረገባቸው የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ወጥ በሆነ መልኩ በየጎዳናው ዳርና በተማሪዎች ማዘውተሪያ ስፍራ እንዲቀመጡ ሊያደርግና ቆሻሻው ሳይዝረከረክ በወቅቱ እየተሰበሰበ የሚወገድ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡

- ❖ ከምግብ ቤቶች የሚመነጩ ቅድመ ምግብና ተረፈ ምግብ ቆሻሻዎች  አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መልኩ ከሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች በመለየት እንዲሰበሰቡ እንዲከማቹና እንዲወገዱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ የዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ግቢዎች የፌደራል አካባቢ ያወጣውን ደረጃ ተከትሎ የተገነባ የቆሻሻ ማስወገጃ/ማቃጠያ ቦታ እንዲእንዲኖራቸው  እና ጥገና በሚያስፈልጋቸው ወቅትም ክትትል በማድረግ አስፈላጊውን ጥገና ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡
- ❖ ከዩኒቨርስቲው ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ በማጓጓዝን በማስወገድ ስራ ላይ የተሰማራው ድርጅት/ሰው ቆሻሻን በወቅቱ እና በአግባቡ ለማስወገድ የሚችል ብቃት ያለው ለመሆኑ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ፍቃድ ያለው እና ህጋዊ መሆኑ ሊረጋግጥ ይገባል፡፡
- ❖ ፈሳሽ ቆሻሻ ከተዘረጋላቸው የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች በመውጣት መሬት ላይ እንዳይፈሱና አካባቢ እንዳያበላሹ ችግር ያለባቸውን ቱቦዎች በመለየት አስፈላጊውን ጥገና በወቅቱ በማድረግ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ከማስተማሪያና ምርምር ቤተ ሙከራዎች የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች የያዙት ንጥረ ነገር በማህበረሰብና በአካባቢ ላይ  ጉዳት እንዳያስከትል አስፈላጊውን ጥንቃቄ /treatment/ በማድረግ ወደ ፍሳሽ ቱቦ የሚገቡ  መሆናቸው ሊያረጋገጥ ይገባል፡፡
- ❖ ከተማሪዎች መኖሪያ ፣ከክሊኒክ ላብራቶሪ፣ ከምርምር ቤተ ሙከራዎች፣ ከምግብ ቤትና ከሽንት ቤቶች የሚወጡ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች በአካባቢ ላይ የሚከረፋ ሽታ ፈጥረው ጠንቅ እንዳይሆኑና ጉዳት እንዳያደርሱ በየቀኑ እንዲፀዱ፣  ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም ለኦዲቱ ሥራው መሳካት የዩኒቨርስቲው የዋና ግቢ እና ቅርንጫፍ ግቢዎች የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ላደረጉልን የስራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ

# የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| ❑ኦ❑ቱ ጭብጥ<br>(Audit Issues) | መስ❑ርቶች<br>(Evaluative Criteria's) |
|---|---|
| 1. .ከዩኒቨርሲቲዎች የሚመነጩ ደረቅ፣ፍሳሽ እና አደገኛ ቆሻሻዎችን ለመያዝና ለማስወገድ ተገቢው የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፣ | 1.1.1 ዩኒቨርሲቲው የተቀናጀ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓትን በመዘርጋት ቆሻሻ መሰብሰቡን፣ መጓጓዙን ፣ እንደተገቢነቱም ጥቅም ላይ መዋሉን፣ መምከኑን ወይም ጉዳት እንዳያመጣ ተደርጎ መወገዱን ማረጋገጥ አለበት፡፡<br>*ምንጭ፣የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ 300/95* |
| | 1.1.2 ዩኒቨርሲቲው የአካባቢ ዘላቂነት (Environmental Sustainability) ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣ College of Natural Sciences newsletter Volume 3,issue 1* |
| | 1.1.3 የዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አያያዝ፣ ማጓጓዝና አወጋገድ በህግ የተቀመጡ መስፈርቶችን ማለትም እንደቆሻሻው አይነት እና ባህር በመለየት የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣ የማጓጓዝ እና የማስወገድ ሊከናወን የሚችልበትን ሁኔታ ግንዛቤ እንዲኖር ማድረግ እና ይህንኑ ተከትሎ መከናወን ይኖርበታል፡፡<br>*ምንጭ፣ Code of practice for wast mgt* |
| | 1.1.4 በዩኒቨርሲቲው ቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ስራ ላይ ለተሰማሩ ሰራተኞች ተገቢው ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣ Code of practice for wast mgt* |
| | 1.1.5 በዩንቨርሲቲው ስለቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ለሰራተኞች፣ ተማሪዎችና ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ 513/99* |
| | 1.1.6 በዩኒቨርሲቲው የቆሻሻ አያያዝ፣ አጓጓዝና አወጋገድ ሰንሰለት ስራዎችን በተመለከተ የስራ ድርሻ እና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ ሊቀመጥ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣ Code of practice for wast mgt* |
| | 1.1.7 የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች የአካባቢ እና ዘላቂነት (Environment and Sustainability) የማስረጽ ኢኒሺየቲቭ አካል የሆነው የሜንስትሪሚንግ ስራ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣ College of Natural Sciences newsletter Volume 3,issue* |
| | .1.8 ዩኒቨርሲቲው በተማሪዎች ከሚመሩ የአካባቢ ዘላቂነት ክበባት ጋር በትብብር የሚሰራበት መንገድ በመፍጠር በሁሉም የአካባቢ ጉዳዮች ቀጣይነት ያላቸው ስራዎች እንዲሳተፉ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣ College of Natural Sciences newsletter Volume 3,issue* |
| 2. ዩኒቨርሲቲዎች ከቢሮዎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ላቦራቶሪዎች፣ የተማሪዎች መኝታ ቤት እና ምግብ ቤቶች የሚመነጩ ደረቅ እና ፈሳሽ እንዲሁም አደገኛ ቆሻሻዎችን የመያዝ፣ የማጓጓዝና የማስወገድ ተግባር ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን መገምገም፣ | 2.ሀ እንደሚመነጩት የቆሻሻ አይነቶች ለማጠራቀሚያ፣ ለማጓጓዣ እና ማስወገጃ የሚያስፈልጉ ቁሰቁሶች ሎሟሉ ይገባል፡፡ |
| | 2.ለ ቆሻሻን የሚመለከቱ ተግባራትን የሚያከናውኑ ሠራተኞች የሚያከናውኑት ተግባራት በግልጽ ተለይቶ በጽሁፍ እንዲደርሳቸው ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| 2.1 የደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ ማጓጓዝ እና አወጋገድ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን መገምገም፣ | 2.1.1 ዩኒቨርሲቲው በተቻለ መጠን የሚያመነጫቸውን ደረቅ ቆሻሻዎች እንደገና በመጠቀም ለኃይል፣ ለማዳበሪያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች ሊውሉ የሚቻልበትን ሁኔታ ሊያመቻችይገባል፡፡ |

| □ኦ□ቱ ጭብጥ (Audit Issues) | መስ□ርቶች (Evaluative Criteria's) |
|---|---|
| | *ምንጭ፣Environmental Policy of Ethiopia* |
| | 2.1.2 በዩኒቨርሲቲው የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ እና ማስወገድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች፣<br>• አስፈላጊው የመከላከያ ቁሳቁስ ሊሟላላቸው ይገባል፡፡<br>• የሚያጓጉዙአቸውን ቆሻሻዎች የሚይዙ የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች እነዲሸፈኑ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣ መልካም ስራ ተሞክሮ* |
| 2.2. የፍሳሽ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ አጓጓዝ እና አወጋገድ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን መገምገም፣ | 2.2.1 ዩኒቨርሲቲው በቂና ተስማሚ የመጸዳጃ ቤት፣ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ዕቃዎችና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች መገልገያዎች በቦታው መዘጋጀታቸውን እንዲሁም ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ አለበት፡፡<br>*ምንጭ፣ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995* |
| 2.3.የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ ማጓጓዝ እና አወጋገድ ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን መገምገም፣ | 2.3.1 ከአደገኛ ቆሻሻ አያያዝ ስርዓት ዋናው መርህ ቆሻሻን ከሚመነጭበት ቦታ ብዛቱን እና አደገኝነቱን መቀነስ በመሆኑ፣ ቆሻሻ ከሚመነጭበት ቦታ የሚቀንስበት መንገድ ሊዘረጋ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣የደረቅ ቆሻሻ መመሪያ* |
| | 2.3.2 ከዩኒቨርሲቲው የተማሪ ክሊኒኮች የሚወጡ አደገኛ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት የተለየ ሥፍራ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣መልካም ስራ ተሞክሮ* |
| 3.ዩኒቨርሲቲዎች ከቢሮዎች፣ የጤና ጣቢያዎች፣ ላቦራቶሪዎች፣ የተማሪዎች መኝታ ቤት እና ከምግብ ቤቶች የሚመነጩ ደረቅ እና ፈሳሽ እንዲሁም አደገኛ ቆሻሻዎችን የመያዝና የማስወገድ ተግባር በብቃት ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን መገምገም፣ | |
| 3.1 የደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ ማጓጓዝ እና አወጋገድ በብቃት ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን መገምገም፣ | 3.1.1 የዩኝቨርሲቲው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ 513/99* |
| | 3.1.2 በዩኒቨርሲቲው ምልክት የተደረገባቸው የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች በየጎዳናው ዳርና በሌሎች የተማሪዎችና ሰራተኞች ማዘውተሪያ ስፍራዎች ሊቀመጡ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡-የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ 513/99* |
| | 3.1.3 የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ሞልቶ ሳይዝረከረክ ቆሻሻው በየወቅቱ መነሳቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡-የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ* 513/99 |
| | 3.1.4.ከምግብ ቤቶች የሚመነጩትን ከምግብ ጋር የተያያዙ ደረቅ ቆሻሻ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ ማለትም የሚሰበሰበውን ቆሻሻ በቀላሉ ለመለየት በሚያስችል መልኩ መሰብሰብ፣ ማጓጓዝና ማስወገድ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፡-የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ 513/99* |
| | 3.1.5 ዩኒቨርሲቲው አግባብነት ያለውን የፌዴራል የአካባቢ ደረጃ በመከተል የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲገነባና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፡፡<br>*ምንጭ፡-የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ 513/99* |
| | 3.1.6 በዩኒቨርሲቲው ለደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ የተገነቡ ማቃጠያዎች ደረጃቸውን የጠበቁና አስፈላጊው ክትትልና ጥገና የሚደረግላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣ከመልካም ስራ ተሞክሮ* |
| | 3.1.7 ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ፣ ጥቅም ላይ በማዋል ወይም በማስወገድ ተግባር ላይ የሚሰራ ማንኛውም ድርጅት/ሰው ከሚመለከተው አስተዳደር አካል በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡ |

| □ኦ□ቱ ጭብጥ<br>**(Audit Issues)** | መስ□ርቶች<br>**(Evaluative Criteria's)** |
|---|---|
| | *ምንጭ፣የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ 513/99* |
| 3.2.የፍሳሽ ቆሻሻዎች አያያዝ፣ ማጓጓዝ እና አወጋገድ በብቃት ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን መገምገም፣ | 3.2.1በዩኒቨርሲቲው የሚመነጩ ፍሳሽ ቆሻሻዎች ከተዘረጋላቸው የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች በመውጣት ከመሬት በላይ እንዳይፈሱ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣ከመልካምስራ ተሞክሮ* |
| | 3.2.2.ከዩኒቨርሲቲው የማስተማሪያና የምርምር ቤተ-ሙከራዎች የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎች ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ ሲገቡ በያዙት ንጥረ ነገር ሊያስከትሉ የሚችሉት ጉዳት እንዳይኖር ስፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣መልካም ስራ ተሞክሮ* |
| 3.3 የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ እና አወጋገድ በብቃት ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን መገምገም፣ | 3.3.1 ከዩኒቨርሲቲው የጤና ተቋማት የሚመነጩ አደገኛ ቆሻሻዎች<br>• አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ በጤና ባለሙያዎች ተለይተው እና ጉዳት እንዳያስከትሉ ተገቢው ህክምና ተደርጎ ለእነዚህ ቆሻሻዎች ማከማቻ ተለይተው በተዘጋጁ ልዩ ማጠራቀሚያዎች ሊቀመጡ ይገባል፡፡<br>• ከዩኒቨርሲቲው የጤና ተቋማት የሚመነጩ አደገኛ ቆሻሻዎች የማሰባሰብ ተግባር በየቀኑ ሊከናወን በማጓጓዝ እና በማስወገድ ተገባራት ወቅትም ጉዳት እንዳያስከትሉም ጥንቃቄ ማድረጉ ሊቀጥል ይገባል፡፡<br>*ምንጭ፣Healthcare waste management directive* |
| | 3.3.2 ሥለታማ ቆሻሻዎች ተለይተው ሊሰበሰቡና የሚከማቹበት ቦታ የሠለጠኑ ባለሙያዎች በሚደርሱበት ብቻ እንዲሆንና ተለይተው እንዲወገዱ መደረግ አለባቸው፡፡<br>ምንጭ፣ Biomedical and Healthcare Waste Management Guidelines |
| | 3.3.4 ከክሊኒኮች ወደ መደበኛው የቆሻሻ ማስወገጃ የሚሄዱ ቆሻሻዎች አደገኛና ሊበክሉ የሚችሉ ቆሻሻዎችን ያልያዙ መሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 3.3.4 ከክሊኒኮች ወደ መደበኛው የቆሻሻ ማስወገጃ የሚሄዱ ቆሻሻዎች አደገኛና ሊበክሉ የሚችሉ ቆሻሻዎችን ያልያዙ መሆናቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |

.